የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩ እና ፲2

1. ጌታ የሚወደው የተባለ አልዓዛር መንደሩ በየት ነበር?
ሀ)ቢታንያ ለ)ኢየሩሳሌም ሐ)ጥብርያዶስ መ)ገሊላ

2. "በቀን የሚመላለስ ቢኖር የዚህን ዓለም ብርሃን ያያልና አይሰናከልም ።" ሲል ቀን የተባለ ምንድነው?
ሀ)መዓልት
ለ)የጌታ ትምህርቱና ዕውቀቱ
ሐ)ብርሃን ያለበት ቦታ ሁሉ
መ)ሀ እና ለ

3. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩ ጨለማ የተባለ ምንድነው?
ሀ)ክህደት ለ)ድንቁርና ሐ)በክርስቶስ አለማመን መ)ሁሉም

4. "የሚያምንብኝም ሁሉ ለዘለዓለም አይሞትም" ማለት
ሀ)ሰው በሥጋ የሚሞተው በጌታ ካላመነ ብቻ ነው
ለ)የሚያምን ሞቱ ጊዜያዊ ሕይወቱ ዘላለማዊ ነው
ሐ)ይህ የተባለው ለአልዓዛር ብቻ ነው
መ)ሁሉም

5. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩ ላይ የተገለጸችው የአልዓዛር እህት ማርያም የትኛዋ ናት?
ሀ)ጌታን ሽቱ የቀባችው ማርያም
ለ)የቀለዮጳ ሚስት ማርያም
ሐ) የዮሐንስ እና ያዕቆብ እናት ማርያም
መ)የጌታችን እናት ማርያም

6. ጌታ ስለ አልዓዛር ሞት ያለቀሰው ለምንድነው?
ሀ)ፍጹም ሰው መሆኑን ለመግለጽ
ለ)እኛም ከሚያዝኑት ጋር እንድናዝን ሊያስተምረን
ሐ)ቀድሞ ባለመምጣቱ ተቆጭቶ
መ)ሁሉም
ሠ)ሀ እና ለ

7. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ አልዓዛር ተኝቷል ሲላቸው ምን ማለቱ ነው?
ሀ)አልዓዛር እንቅልፍ ወስዶታል
ለ)አልዓዛር ንቃተ ሕሊና ውስጥ ገብቷል
ሐ)አልዓዛር ሞቷል
መ)ሁሉም

8. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አላዓዛርን ከሞተ በስንተኛው ቀን አስነሳው?
ሀ)በሦስት ቀኑ ለ)በሁለት ቀኑ ሐ)በአራት ቀኑ መ)በስድስት ቀኑ

9. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፩ ላይ "እኛም ከእርሱ ጋር እንሞት ዘንድ እንሂድ " ብሎ የተናገረው ማን ነው?
ሀ)ቶማስ ለ)ዲዲሞስ ሐ)ማቴዎስ መ)ሀ እና ለ

10.ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ እና ሕይወት መሆኑን በምን አሳየን?
ሀ)አልዓዛርን ከሞት በማስነሳት
ለ)ትምህርቱን በደንብ በማስተማር
ሐ)ተአምራትን በማድረግ
መ)መልስ አልተሰጠም

11. ጌታችን ተአምራትን ያደረገው ለምንድን ነው?
ሀ)ብዙዎች በእርሱ እንዲያምኑ
ለ)ሰዎችን አዝኖ እራርቶላቸው
ሐ)ሰዎችን ከችግር ለማውጣት
መ)ሁሉም

12.ጌታችን በማልቀሱ አይሁድ ምን አስተዋሉ?
ሀ) ምን ያህል አልዓዛርን እንዳልወደደው
ለ) ምን ያህል አልዓዛርን እንደወደደው
ሐ)የጌታችን ትምህርት እውነት እንደሆነ
መ)ሁሉም

13."ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ ስለሕዝቡ አንድ ሰው ቢሞት ይሻለናል" ያለውቀያፋ በማን ተነሳሽነት ነው?
ሀ)በመንፈስ ቅዱስ ለ)በዲያብሎስ ሐ)በራሱ መ)ሁሉም

14.አይሁድ አልዓዛርን ለምን ጠሉት?
ሀ)ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱ ላይ ያደረገው ተአምር ብዙዎችን እንዲያምኑ ስላደረገ
ለ)ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ስለበላ
ሐ)በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመነ
መ)ሁሉም

15. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ "ጌታ ኢየሱስን ልናየው እንወዳለን" ያሉት እነማን ናቸው?
ሀ)ፊሊጶስ እና እንድርያስ
ለ)የግሪክ ሰዎች
ሐ)ስንዴን የሚዘሩ ገበሬዎች
መ)መልስ አልተሰጠም

16."እኔም ከምድር ከፍ ከፍ ካልሁ ሁሉን ወደ እኔ እስባለሁ" ይህንን የተናገረው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለምንድን ነው?
ሀ)ስለልደቱ ለ)ስለትንሳኤው ሐ)ስለስቅለቱ መ)ስለዳግም ምጻቱ

17. ሐዋርያው ዮሐንስ የፃፈው ወንጌል ላይ የሆሳዕና ታሪክ በማቴዎስ እና በማርቆስ ወንጌል ከተፃፈው በምን ይለያል?
ሀ) የዮሐንስ ወንጌል ስለሆሳዕና አይናገርም
ለ) የዮሐንስ ወንጌል ሁለት ደቀመዛሙርት መላካቸውን አያነሳም
ሐ) የዮሐንስ ወንጌል ሕዝቡ የዘንባባ ዝንጣፊ እንዳመጡ አይናገርም
መ)ሁሉም

18. 300 ዲናር ያወጣል የተባለው የምን ሽቱ ነው?
ሀ)የጣፋጭ ሽቱ ለ)የአልባጥሮስ ብልቃጥ ሐ) የናርዶስ መ)ለ እና ሐ

19. ይሁዳ ለምን ሽቱው ተሸጦ ለድሆች እንዲሰጥ ፈለገ?
ሀ)ለጌታችን ሽቱ አይገባም ብሎ
ለ)ለድሆች አስቦ
ሐ)ከሚገባው ገንዘብ ይሰርቅ ስለነበር
መ)መልስ አልተሰጠም

20. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሙዳዩን የመጠበቅ ኃላፊነት ለማን ሰጠ?
ሀ)ቀራጭ ለነበረው ሌዊ
ለ)ለዲዲሞስ
ሐ)ለአስቆሮቱ ይሁዳ
መ)ለማንም አልሰጠም

21."ሕዝቡ ሁሉ ከሚጠፋ አንድ ሰው ስለ ሕዝቡ ይሞት ዘንድ... " ያለው ማን ነበር?
ሀ) ሐና ለ) ቀያፋ ሐ) ይሁዳ መ) ሁሉም

22. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 11 ላይ ጌታ ኢየሩሳሌምን ትቶ የሄደው ወዴት ነው?
ሀ) ገሊላ ለ) ኤፍሬም ሐ) ሮሜ መ) ደብረ ታቦር

23. ቢታንያ ማለት ምን ማለት ነው?
ሀ)የእንጀራ ቤት ለ)የበለስ ቤት ሐ)መድኃኒት መ)መልሱ የለም

24. በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 12 ላይ ለጌታ ራት የተደረገው በማን ቤት ነበር?
ሀ) አልዓዛር ለ) ስምዖን ዘለምጽ ሐ)ስምዖን ዘአምድ መ) ስምዖን ቀነናዊ

25. ጌታችን አልዓዛርን ከሞት ሲያስነሳው “አልዓዛር አልዓዛር ና ውጣ” ብሎ ሁለት ጊዜ ስሙን የጠራው ለምንድን ነው?
ለዕብራውያን ድጊመ ቃል ልማድ ስለሆነ
የሥጋህ እና የነፍስህ ፈጣሪ ነኝ ሲል
ሥጋን ከመቃብር ነፍስን ከገሃነም ሲጠራ
ሁሉም መልስ ናቸው